# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 115 ሐምሌ 22 ቀን 2002 ገጽ 1


**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**“የጋራ ውርደት እንዲያክትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## ዘረኛውና አምባገናዊው የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንን ስርጭት እንደገና ማፈኑ ታወቀ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት (ኢሳት) በዚህ ሳምንት እንደገና መታፈኑን እና ስርጭቱ መቋረጡን ድርጅቱ በለቀቀው መግለጫ አስታወቀ።

መግለጫው አፈናውን የሚያኪሄደው ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ስለመሆኑም ድርጅቱ ማስረጃ እንዳለው ገልጿል። አገዛዙ ኢሳት ቴሌቪዥንን ለማፈን በሚያካሄደው ጥረት በገዛ ቁጥጥሩ ስር የሚገኘውን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት የሳተላይት ስርጭትም አብሮ ማፈኑ ታውቋል። ኢሳት በመግለጫው ከራሱ ስርጭት በተጨማሪ የሌሎች ድርጅቶች ስርጭቶችም በአፈናው እንደተጎዱ ገልጾ፤ በዚህ እኩይ ተግባር ከተጎዱ አካላት ጋር በመተባበር ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚጥር ገልጿል።

የወያኔ አገዛዝ ኢሳት መቋቋሙን እንደተረዳ ከቻይና የማፈኛ መሳሪያ በብድር ማስመጣቱን እና የድርጅቱ ስርጭቶች እንደጀመሩም ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል በማፍሰስ እያፈነ እንዳለ አዲስ ነገር ኦንላይን የተባለውን ድረ-ገጽ በመጥቀስ ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል።

## ኢትዮጵያውያን በኤሌክትሪክ ሃይል እጦት እየተንገላቱ ባሉበት የወያኔ አገዛዝ ለጎረቤት አገሮች የኤሌክትሪክ ሃይል ለመሸጥ ዝግጅቱን መፈጸሙን ገለጸ

አዲስ አበባን ጨምሮ በበርካታ የአገሪቱ ክፍላት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና የንግድ ድርጅቶቻቸው በኤሌክትሪክ ሃይል እጦት ምክንያት እየተንገላቱ ባሉበት ወቅት የወያኔ አገዛዝ የኤሌክትሪክ ሃይል ለጎረቤት አገሮች ለመሸጥ ዝግጅቶች አጠናቅቄያለሁ ማለቱ ተዘግቧል።

አፍሪካን ፕሬስ ኤጀንሲ የተባለ የዜና አውታር ማክሰኞ እለት ባወጣው ዘገባ፣ እንደታቀደው ከሄደ ለሱዳን፣ ለኬንያ እና ለጅቡቲ የሚደረገው የኤሌክትሪክ ሃይል ሽያጭ በሚቀጥለው የፈረንጆች አመት ይጀምራል። ያንን ለማድረግ የሚያስችለው የኤሌክትሪክ መስመር ግንባታ መፈጸሙን አገዛዙን ጠቅሶ ዘግቧል።

በአዲስ አበባ እና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች አንዳንድ ጊዜ በየቀኑ ለሰዓታት የሚቋረጠው የኤሌክትሪክ ሃይል የንግድ ስራዎችን እያስተጓጎለ እና ዜጎችን ለእንግልት እየዳረገ መቆየቱን በተደጋጋሚ መዘገባችን ይታወሳል። በአገር ቤት ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል እጥረት እያለ አገዛዙ ለውጭ አገራት ለመሸጥ የተነሳበትን ምክንያት አስመልክቶ አስተያየታቸውን (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## እንደ ወያኔ ያሉ አፋኝ አገዛዞች የህዝብ ገንዘብ በመጠቀም በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ እያደረጉ ነው ተባለ

ኒውስዊክ የተባለው ታዋቂ የአሜሪካ ጋዜጣ ሰሞኑን ባወጣው ጽሁፍ እንደ ወያኔ ያሉ አፋኝ አገዛዞች ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በማፍሰስ በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ እያደረጉ ነው ብሏል።

የተለያዩ አምባገነናዊ አገዛዞች በአሜሪካን አገር የሚገኙ የሎቢ ድርጅቶችን በከፍተኛ ገንዘብ በመቅጠር የአሜሪካ ህግ አውጪ አካል እና አስተዳደር እነሱን በሚመለከት ጠንካራ አቋሞች እንዳይወስዱ ሲያመክኑ ቆይተዋል ብሏል ጋዜጣው በድረ-ገጹ ባወጣው ትንታኔ። እነዚህ አገዛዞች ከፍተኛ መጠን ያለው የህዝብ ገንዘብ እየተጠቀሙ የሚሟገቱላቸው ድርጅቶች ሲቀጥሩ፤ በየአገሮቻቸው እነሱን የሚቃወሙት ድምጾች ግን ያንን የሚቋቋም ጉልበት ለማሰባሰብ አይችሉም። የዚህ ውጤትም የወንበዴዎች በዋሽንግተን ሰሚ ማግኘት እና የተቃዋሚዎቻቸው ድምጽ መታፈን ሆኗል ሲል ኒውስዊክ ገልጿል።

ጋዜጣው፥ በዚህ ትንታኔው የወያኔ አገዛዝ ቅጥረኛ የሆነውን ዲ.ኤል.ኤ. ፓይፐር የተባለ ድርጅት ጠቅሷል። አብዛኛው ህዝቧ በድህነት የሚማቅቀውን ኢትዮጵያን በጉልበት ተቆጣጥሮ ያለው ወያኔ ዲ.ኤል.ኤ. (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ “በፌዴሬሽን ስም የሚነግድ” ነው ሲሉ የአፋር ህዝብ ፓርቲ መሪ ገለጹ

የአፋር ህዝብ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ አሎ አላዳይስ ከግንቦት 7 ድምጽ ራድዮ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ የወያኔ አገዛዝ በፌዴሬሽን ስም የሚነግድ እንጂ እውነት ፌዴሬሽን እንዲሰራ የሚፈልግ አይደለም ብለዋል።

አቶ አሎ እሁድ እለት ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ቃለ መጠይቅ፥ የአፋር ክልል የራሱ የሆነ መንግስት አለው ማለት የማይቻልበት ሁኔታ እንዳለ ገልጸዋል። ተሰሚነት ያላቸው ታዋቂ ግለሰቦች እና ምሁራን ከፖለቲካ ምህዳሩ ተገለው፤ የወያኔ ተላላኪ የሆኑ ካድሬዎች ክልሉን እያመሱት ነው ብለዋል።

በአሁኑ ሰዓት በአፋር ያለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከህዝቡ ተቀምቶ ከወያኔ ጋር ትስስር ወዳላቸው ኢንቬስተሮች ተዛውሯል የሚሉት አቶ አሎ፣ ህዝቡ ከለም መሬቱ እየተፈናቀለ ወደ በረሃ እየተገፋ ነው ብለዋል። ከዚህ ቀደም በእርሻ እና በጨው አምራችነት ይተዳደሩ የነበሩ የአፋር ማህበረሰቦች መሬታቸውን መቀማታቸው፤ ከጦርነት የተነሳ የተስተጓጎለው ንግድ እና ከድርቅ የተነሳ የተዳከመው የእንስሳት እርባታ ተደማምረው ህዝቡን ለረሃብና እንግልት መዳረጋቸው ታውቋል። ይህንን ሁኔታ በሚመለከት ጥያቄ የሚያነሱ ዜጎችም ከነሳቸው እንደጠላት እንደሚፈረጁ ሊቀመንበሩ ገልጸዋል።

አቶ አሎ ጨምረውም፥ የኢትዮጵያ መንግስት በአንድ ብሔረሰብ ቁጥጥር ስር ነው ያሉ ሲሆን፤ በፌዴሬሽን ሊኖር የሚገባው የስልጣን ክፍፍል በአገሪቱ ውስጥ እንደሌለ እና ወያኔ በአፋር ክልል ህዝቡ እራሱን እንዲመራ ሊፈቅድ ይቅርና የህዝቡን ማንነት ለመለወጥ ጥረት እያደረገ እንደሆነ ተናግረዋል።

## ወያኔ በአዲስ አበባ ስራዬን አበላሽተውብኛል ያላቸውን ካድሬዎቹን ማባረሩ ተዘገበ

ገዢው ፓርቲ ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ ባካሄደው ግምገማ ከውስጥ ሆነው ስራዬን አበላሽተውብኛል ያላቸውን ካድሬዎቹን ከፓርቲ ማባረሩን አዲስ ነገር ኦንላይን የተባለው ድረ-ገጽ ዘግቧል።

የወያኔ የአዲስ አበባ ቢሮ ሃላፊ በሆነው ሬድዋን ሁሴን በተመራው በዚህ ግምገማ ላይ፥ በሚቀጥለው ምርጫ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት ካገኙት ያነሰ ድምጽ በሚያገኙበት ሁኔታ ላይ ውይይት ተደርጓል። ግንቦት 15 ቀን ተቃዋሚዎች በአዲስ አበባ ከሁለት መቶ ሺህ በላይ ድምጽ ማግኘታቸው በአጽንዎት መዳሰሱን ድረ-ገጹ ዘግቧል።

የግምገማው አላማ ወያኔ ከውስጥ ሆነው ስራዬን አበላሽተውብኛል፤ እንዲሁም አድርባዮች ናቸው የሚላቸውን ለይቶ ለማባረር እንደሆነ ዘገባው ያሳየ ሲሆን፤ በዚህም መሰረት ውስጥ ለውስጥ ተቧድነዋል፣ የጥቅም መረብ መስርተዋል ተብለው የተወነጀሉት መባረራቸውን ገልጿል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ ከውጭ አገራት ቤተክርስቲያናት ጋር በሚያደርጉት ድርድር የወያኔን ፈቃድ የማስፈጸም ተልእኮ ይዘው እንደተነሱ ታወቀ

የወያኔ አገዛዝ የውጭ አገር ቤተክርስቲያናትን በቁጥጥሩ ስር ለማዋል የያዘውን እቅድ ለማስፈጸም ፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ እንቅስቃሴ መጀመራቸውን ለቤተክርስቲያኒቱ አመራር ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ በላኩት መረጃ አስረድተዋል።

ከአገዛዙ ጋር ጥብቅ የሆነ የጥቅምና የመንደር ልጅነት ትስስር እንዳላቸው የሚታወቀው አቡነ ጳውሎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርክ ሆነው ከተሰየሙ በኋላ በውጭ አገራት ያሉ አድባራት ከአገር ቤቱ ሲኖዶስ መለየታቸው እና በተሰደዱት አቡነ መርቆርዮስ አመራር ስር መቅረታቸው ይታወቃል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህን ክፍፍል ለማስወገድ እና ቤተክርስቲያኒቱን እንደገና አንድ ለማድረግ ድርድር ተጀምሯል።

በውጭ አገራት እና በአገር ቤቱ ሲኖዶስ ውስጥ ያሉት አንዳንድ አባቶች ይህንን ድርድር የሚያካሄዱት በሙሉ ልብ እርቅን በመሻት ቢሆንም፤ ፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ ግን አጋጣሚውን በመጠቀም የወያኔን ተልኮ ለማስፈጸም እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ናቸው የሚል መረጃ ለዝግጅት ክፍላችን ደርሷል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛ የትምህርት ሥርዓትን ለመቀየር ዘረኛውን አገዛዝ ከሥልጣን ማባረር ግድ ነው!!!

ትምህርት የእውቀት አድማስን ካላሰፋ፤ አዳዲስ ክህሎቶችን ካላሳወቀ፤ የእለት ከእለት ኑሮን ካላሻሻለ እና አዎንታዊ የባህርይ ለውጥ ካላመጣ ፋይዳው እምን ላይ ነው?

የወያኔ የትምህርት ሥርዓት ከላይ ከዘረዘርናቸው ውስጥ ለአንዱም የተዘጋጀ አይደለም። ወያኔ ትምህርት ቤቶችንና ዩኒቨርስቲዎችን ከእውቀትን መገበያያነት ይልቅ እጅግ ኋላቀር የሆነ ዘረኛና ጎጠኛ አስተሳሰብ ማራቢያና ማሰራጫ ተቋማት አድርጎዓቸዋል። ዛሬ በወያኔ መዳፍ ውስጥ ባለችው ኢትዮጵያ ውስጥ ተማሪዎች ዘራቸው መታወቂያቸው እንዲሆን ተደርጓል። እንደድሮ ከሰሜኑም ከደቡብም፣ ከምሥራቅም ከምዕራብም የመጡ ወጣቶች የተደባለቁባቸው የጥናትም ሆነ የጨዋታ ቡድኖች በዛሬዎቹ ዩኒቨርስቲዎች ማግኘት አይቻልም። እያንዳንዱ ተማሪ ከጎጡ ልጅ ጋር ብቻ እንዲቧደን፤ ከሌላ አካባቢ የመጣውን የክፍል ባልደረባውን በጥርጣሬ፣ ከዚያም አልፎ በጠላትነት እንዲመለከት ተደርጓል። ከዚህ ሁሉ በላይ አሳሳቢ የሆነው ጉዳይ ደግሞ ወያኔ ከትግራይ ክልል የመጡ ተማሪዎችን ከሌሎች ወንድሞቻቸው ለመነጠል የሚሠራው የተቀናጀ ሥራ ነው። እነዚህ ወጣቶች በሌሎች የክፍል ባልደረቦቻቸው ላይ የበላይነትና የሁሉ-አውቅነት ስሜት እንዲኖራቸው የሚያበረታቱ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። ይህ በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በግልጽ የሚታይ ጉዳይ ሆኗል። በየካምፓሱ የተቋቋሙት "የትግራይ ተማሪዎች ማኅበራት" ሥራቸው ይህንን ማስፈጸም ነው። አንድ የትግራይ ወጣት በግል ይህንን ቢቃወም "ብሄራዊ" ግዴታውን እንዳልተወጣ ከሃዲ እንዲታይ ይደረጋል። በአንፃሩ ደግሞ የሌሎች ክልሎች ተማሪዎች የታዘዙትን በፈጸሙ መጠን ጉርሻ እየተሰጣቸው ለታማኝ ሎሌነት ይዘጋጃሉ። ለእነሱም የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የሶማሌ፣ ... ወዘተ ማኅበራት ተቋቁመውላቸዋል። የዛሬዎቹ ዩኒቨርስቲዎቻችን ጥቂቶች ገዢነትን፤ ብዙዎች ደግሞ ባርነትን የሚለማመዱባቸው የአገዛዝ ማሰልጠኛ ቦታዎች ሆነዋል።

ከክህሎት አኳያም ቢሆን ወጣቶቻችን የሚማሩት ውሸትን፣ ጉራንና ትዕቢትን ሆኗል። ኑሮን ለማሸነፍ አንድም ከምርጥ ዘር መወለድ አሊያም ለምርጥ ዘር ማደግደግ መቻል እንጂ በትምህርት መጎበዝ ፋይዳ እንደሌለው እዚያው ዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ የሚያዩት ሃቅ ሆኗል።

አሁን በሥራ ላይ ያለው የትምህርት ሥርዓት ኢትዮጵያን የሚጠሉ፤ በንዋይና ሥልጣን ፍቅር የታወሩ፤ ኢትዮጵያንም በወረራ እንደያዟት አገር በጥላቻ የሚገዙ ወያኔዎች የገነቡት ነው። ይህ ሥርዓት የፈጠራቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም እነዚሁ ሰዎች የሚዘውሯቸው ወፍጮዎች ናቸው። በተለይ አዳዲሶቹ ዩኒቨርስቲዎች ከትምህርት ጋር ፈጽሞ የሚተዋወቁ አይመስልም። ዩኒቨርስቲዎቹ ዘረኝነትን ለማስፋፋት ተብለው የተቋቋሙ ተቋማት ናቸው።

ለዚህም ነው ዛሬ ዛሬ በተማሪዎች መካከል በምንም ጉዳይ ግጭት ቢነሳ ወዲያውኑ በዘር ወደተቧደኑ ቡድኖች ጠብ የሚያመራው። ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ "እከሌ እና እከሌ ተጣሉ" ማለት ተረስቷል። "ትግሬና ኦሮሞ ወይም ትግሬና አማራ ተጣሉ" ነው የሚባለው። ጅማ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ለተሰነዘረ ቡጢ መቀሌ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፤ ለሱ ደግሞ ሃረማያ ውስጥ አፀፋ ይከተላል። ወዲያውኑ የሃዋሳ፣ የወላይታ፣ የሰመራ ዩኒቨርስቲዎች ተማሪዎች የጠቡ አካል ይሆናሉ ። አንድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የተነሳ ጠብ በአንድ ቀን አገሪቷን ያዳርሳል። የዘመነ ወያኔ የተማሪዎች ጠብ ዘር እንጂ ፊት አይለይም። ይህ አገራችን ወደየት እየሄደች እንደሆነ የሚያሳይ ሁነኛ አመላካች ነው። ዛሬ በዚህ ጉዳይ ላይ እርምጃ ካልወሰድን ነገ ሊረፍድ ይችላል።

ደግሞስ ይኸ ሁሉ መከራ ለየትኛው ትምህርት ነው? የትምህርት ጥራት እጅግ ከመውደቁ የተነሳ "ጭራሹን ትምህርቱ ባይሰጥ ይሻል ነበር?" እሚያስብል ደረጃ ላይ ደርሷል። ወያኔ "ትምህርትን አስፋፋሁ!" ለሚለው ጉራው እና በዚህም ምክንያት ለሚገኘው የእርዳታ እርጥባን ሲል ብዛት ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ የትምህርት ጥራትን ጉዳይ ፈጽሞ ቸል ብሎታል። ለወያኔ የጥራት ጉዳይ ደንታው አይደለም። በዚህም ምክንያት "ወጣቶቻችን ምን ተምረው እየወጡ ነው?" የሚለው ጉዳይ በእጅጉ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል።

በዘረኛ የትምህርት ሥርዓት አማካይነት በአገራች ወጣት ላይ እየደረሰ ያለው በደል ጠልቆ እንዲሰማን ሁለት ተጨማሪ ነጥቦችን ማንሳት ያስፈልጋል።

አንደኛ፣ የወያኔ ቱባ ባለሥልጣናት ልጆች በምርጥ የግልና የውጭ አገራት ተቋማት ተቀማጥለው የሚማሩ መሆናቸው ነው። ይህ ተግባር ወያኔዎች የገነቡት የትምህርት ሥርዓት ለራሳቸው ልጆች የማይመርጡት መሆኑን ያረጋግጥልናል። በሌላ በኩል ደግሞ በወያኔ እምነት ልጆቻቸው የነሱ ሥልጣን ተረካቢዎች ናቸውና እየተፈጠረልን ያለው አዲስ የገዥ መደብ ምን ያህል ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሃቅ የተነጠለ፤ እንዲያውም ከሌላ ፕላኔት የመጣ የሚመስል እንደሆነ ልብ ይሏል።

ሁለተኛ፣ በክልሎች መካከል ልዮነትን የሚያሰፋ የትምህርት ሥርዓት ያለን መሆኑ ነው። ለምሳሌ የሶስተኛ ሳይክል ትምህርት በትግራይና በሌሎች ክልሎች አንድ አይነት አይደለም። ሂሳብና እንግሊዝኛ ቋንቋ በመጠቀማቸው መጠንም በእጅጉ ይለያያሉ። በዚህም ምክንያት ከተለያዩ ክልሎች የሚመጡ ተማሪዎች ዩኒቨርስቲ ወይም ኮሌጅ ውስጥ ሲገናኙ በተመጣጣኝ ደረጃ ላይ አይደሉም። ይህ ከዘረኝነትም በላይ ነው።

ይህ መርዛማ የሆነ የትምህርት ፓሊሲ ምንጩ የወያኔ ባህርይ ነው። ስለሆነም ወያኔ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ እየባሰ ይሄድ እንደሆነ እንጂ ሊሻሻል አይችልም።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ እየተገበረው ያለው ዘረኛ የትምህርት ፓሊሲ የሚያመጣውን ዘላቂ ጉዳት በጥልቀት ይረዳል። ይህ የትምህርት ፓሊሲ እስካሁን ያደረሰዉን ጥፋት ለማስወገድ እጅግ ብርቱ ፈተና እንደሚጠብቀንም ያውቃል። ከዚህም በላይ በሥራ ላይ እንዲውል ከፈቀድን ደግሞ ፈጽሞ የማይጠገን ጉዳት ሊያመጣብን ይችላል። ስለሆነም አቋራጩ መፍትሄ ወያኔን አስወግዶ በምትኩ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በእኩል የሚያስተናግድ፤ ሁሉንም የሚጠቅም፤ እውቀትን፣ ክህሎቶችንና መልካም ባህሪያትን የሚያጎናጽፍ የትምህርት ሥርዓት መዘርጋት ነው። ዘረኛ የትምህርት ሥርዓትን ለማስወገድ ዘረኛውን አገዛዝ ከሥልጣን ማባረር ግድ ነው!!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## በጂጂጋ ከተማ አንድ ወጣት ዜጋ በወያኔ ጦር ተገድሎ መንገድ ላይ መጣሉ ተዘገበ

ሐምሌ 14፣ 2002 ቀን በጂጂጋ ከተማ አንድ ወጣት ልጅ በአካባቢው በሚገኘው የወያኔ ጦር ተገድሎ በከተማው በሚገኝ እስር ቤት ፊት ለፊት መጣሉን ኦጋዴን ኦንላይን የተባለው ድረ-ገጽ ዘግቧል።

ሃሰን የሱፍ አሊ የተባለው ወጣት ከሶስት አመታት በፊት ደገሃቡር ከሚገኝ ቡድህሌ የተባለ መንደር ተወስዶ እስር ቤት እንደቆየ ድረ-ገጹ የገለጸ ሲሆን፤ ከመገደሉ በፊት በወያኔ ጦር ሰፈር መታየቱንም አስታውቋል። ወጣቱ የተገደለው ታንቆ እንደሆነ የሚያሳይ ምልክት ከአስከሬኑ ጋር መታየቱንም ኦጋዴን ኦንላይን ጠቅሷል። የአካባቢው ሰዎች አስከሬኑን እንዳይቀብሩ መከልከላቸውን እና ይህም በርካቶችን ማስቆጣቱን ድረ-ገጹ አክሎ ገልጿል።

የዚህን ዜና ጥቆማ ለዝግጅት ክፍላችን ያደረሱ ስማቸው እንዳይጠቀስ የሚሹ ኢትዮጵያዊ፣ ይህ ሁኔታ የደርግን ዘመን እንዳስታወሳቸው ተናግረዋል። የቀድሞው ወታደራዊ አገዛዝ አብዮት ጠባቂዎች፥ ጸረ አብዮት የሚሏቸውን ኢትዮጵያውያን እየገደሉ በየመንገዱ እንደሚጥሉ እና ሰዎች እንዳይቀብሯቸው እንደሚከለክሉ ይታወሳል።

የዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ ጦር የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባርን (ኦብነግ) በመዋጋት ስም በሶማሌ ክልል ንጹሃን ዜጎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ መብት ረገጣን እንደሚፈጽም ይታወቃል። ከሶስት አመታት በፊት ኦብነግን በመዋጋት ስም ወደ ክልሉ የገባው ጦር የጦር ወንጀል መፈጸሙን ሂውማን ራይትስ ዋች የተባለው የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ቡድን መግለጹ ይታወሳል።

## ኢትዮጵያውያን በኤሌክትሪክ ሃይል እጦት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እንዲሰጡን የጋበዝናቸው ግለሰብ፥ ምናልባት አገዛዙ አገር ውስጥ ላለው ህዝብ አገልግሎቱን በማቅረብ ከሚያገኘው ገንዘብ ይልቅ ለውጭ አገራት በመሸጥ ሊያገኝ የሚችለውን የውጭ ምንዛሬ በማሰብ እንደሆነ ግምታቸውን ገልጸዋል።

ግለሰቡ ጨምረውም፥ "ምንም እንኳ ይህ ከላዩ ሲታይ የበለጠ ትርፍ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም አካል የሚያደርገው ነገር ቢመስልም የአንድ አገር መንግስት ነኝ ከሚል አካል ግን የማይጠበቅና ሃላፊነት የጎደለው፤ ቀድሞውኑ ቀጫጫ የነበረውን የአገሪቱን ኢንዱስትሪ የሚያመነምን እና የሚያጠፋ ነው" ብለዋል። "ይህ ድርጊት አገዛዙ እንደሚለው ከተሳካ፣ ወያኔ በአገሪቷ ላይ የሚያካሄደው ዘረፋ አካል ተደርጎ መታየት አለበት፤ ለአገዛዙ በአጭር ጊዜ ውስጥ ገንዘብ የማሰባሰብ እንጂ ኢትዮጵያን የመጥቀም አላማ ይዞ የተነሳ አይደለም" ብለዋል።

## ወያኔ በአዲስ አበባ ስራዬን አበላሽተውብኛል . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የወያኔ አገዛዝ በተለይም ባለፉት አምስት አመታት ድጋፍ ለማግኘት ሲል ሙስና በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ እንደፈቀደ እና በርካታ አድርባዮችን በማዝመት በህዝቡ ላይ ከፍተኛ አፈናን ሲያካሄድ መቆየቱ ይታወቃል። ጉዳዩን በሚመለከት አስተያየታቸውን የለገሱን ግለሰብ፥ "እራሱ እንዲስፋፋ በፈቀደው አድርባይነት አሳቦ እነዚህን ሰዎች መልሶ ማባረሩ በግንቦት 15ቱ ምርጫ ተብዬ የፈለገውን ውጤት ካገኘ በኋላ ሸክም ለማውረድ ነው" ካሉ በኋላ፣ ሁኔታው "አብዮት ልጆቿን ትበላለች" የሚለውን አባባል እንዳስታወሳቸው ገልጸዋል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# እየደመቀ የመጣው የሕዝብ የተባበሩ እሪታና ሊሰጠው የሚገባ ምላሽ

በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የጥናትና ምርምር ኮሚቴ የተዘጋጀ: ሐምሌ 2002 (ክፍል 4 )

### 5.2.2 በነፃና ገለልተኛ ሚድያዎች የሚሰራ

- የድርጅት መሪዎችን፣ ባላሙያዎችን፣ ታዋቂ ግለሰቦችን እና ተቆርቆሪ ዜጎችን በማነጋገር የትብብሩ አድማስ እንዲሰፋ መጣር፤
- ሕዝባዊ የመገናኛ ብዙሃን የትብብር መድረኮችን አመቻች እንዲሆኑ ማበረታታት፤
- የትብብርን የስነ ምግባር ደንብ ሕዝብ በሚገባ እንዲያውቀው ማድረግ፤
- ይህንን ደንብ በመጣስ ችግር ፈጥረው፣ ራሳቸው ተስማምተው ያቆሟቸውም የሽምግልናና የውሳኔ ሰጪ ቦርዶቾች ጥፋተኛ ያደረጓቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች ሕዝብ እንዲያውቃቸው ማድረግ፤
- የሽምግልና እና የውሳኔ ቦርዶችን ውሳኔ በሕዝብ እንዲታወቁ ማድረግ

### 5.3 በማኅበረሰባችን ውስጥ መሰራት የሚገባው

- ትብብርን የሚያደናቅፉ፣ ትብብሩ ውስጥ ከገቡ በኋላ ቃልኪዳን ያፈረሱ፤ ችግር መፍቻ ይሆናል ብለው ተስማምተው ያቆሙተን ተቋም ውሳኔ አልቀበልም ብለው የሚያፈንግጡ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ማግለል፤
- ከዚህ ቀደም እንደነበረው ጥፋተኛና ጥፋተኛ ያልሆነውን በይሉኝታና በአድርባይነት በእኩል ከሚስተናገዱበት ጎጂ ባህል ተላቆ ጥፋተኞች የሚወቅሱበት፤ በጎ የሰሩትን የሚያበረታቱበት ባህል እንዲዳብር መጣር፤
- የሲቪክ ማኅበራት ከገባንበት ሲኦል እንዳንወጣ የሚያደናቀፉንን ጎጂ ባህሪዎችንና ዝንባሌዎችን የመታገል፤ ዲሞክራሲያዊ ባህሎችን የመገንባት ግንባር ቀደም ኃላፊነት እንዲወስዱ ማበረታታት።

### 5.4 ሁሉንም ሊያሰማሙ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ትብብር ማድረግ

- የአገራችን የፖለቲካ ሂደት ይህንን ችግር አቃሎታል። ሁሉንም የሚያስማማው የመተባበሪያ አጀንዳ አንድ ብቻ ነው። **አሁን የትብብሩ ዓላማ የፖሊሲ አንድነት ለማምጣት ሳይሆን ሕዝብ እነዚህን የፖሊሲ ልዩነቶች በነፃነት አዳምጦ በነፃነት የሚበጀውን እንዲመርጥ ማስቻል ነው።** የትብብሩን መሰረታዊ ዓላማ ይህንን በማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደፊት የምርጫ እድል አግኝቶ ውሳኔ በሚሰጥባቸው ጉዳዮች ላይ የፖለቲካ ድርጅቶች ትብብር አፍራሽ ወደሆነ አላስፈላጊ ንትርክ እንዳይገቡ ማድረግ ይቻላል።
- ሕዝብ ለፖለቲካ ድርጅቶች በነፃነት ድምጹን በመስጠት የስልጣንን ባለቤትነት እንዲወስን ለማድረግ በተደረሰ ስምምነት የሚጀመር መተባበር ለዚህ ዴሞክራሲያዊ ሂድት እንቅፋት የሆነውን ወያኔን ለማስወግድ ድርጅቶች የሚጠቀሙበት የትግል ስልት የመለያያ ነጥብ እንዳይሆን ማድረግ ይቻላል። ዓላማውን እንዲህ ግልጽ አድርጎ የሚነሳ ትብብር ሰላማዊና ህጋዊ፣ ስላማዊ ግን ህጋዊ ያልሆነ፣ ሰላማዊና አመጽን ያካተተ ሁለገብ ትግል ወይም የአመጽ ትግል ብቻ እናደርጋለን በሚሉ ድርጅቶች መካከል እስካሁን የነበረውን ልዩነት አጥቦ ሁሉም በአንድ ላይ ተባብረው የሚታገሉበትን ሁኔታ ይፈጥራል።
- እነዚህን በጣም ቀላል የሆኑ የትብብሩን አላማዎች ሕዝብ በቀላሉ የሚረዳቸው ብቻ ሳይሆን በትብብር ውስጥ በርካታ ፖለቲካዊና ፖለቲካዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንዲሳተፉ የሚስቡም ናቸው። ከትብብር ለማፈንገጥ በር ስለማይከፍቱ ትብብሮች ግባቸውን እንዲመቱ የተሻለ እድል ይሰጣቸዋል።

## 6 ግቡን ሊመታ የሚችል ታላቅ የመተባበር እንቅስቃሴ እንዴት መጀመርና ማስተባበር እንችላለን?

### 6.1 እንደ መንደርደያ

ከተራ ቁጠር 5.2 እስከ 5.4 የተዘረዘሩት ተግባራት በሚገባ ከተፈፀሙ ከላይ ያቀረብነውን ጥያቄ የመመለሱ ሥራ ከግማሽ በላይ ተጠናቋል ማለት ይቻላል።

ከዚህ ቀጥሎ "ግቡን ሊመታ የሚችል ታላቅ የትብብር እንስቃሴ እንዴት ማስተባበር ይቻላል" በሚል የቀረበውን ግዙፍ ጥያቄ በተለያዩ ንኡስ ርዕሶች በመከፋፈል ለመመለስ እንሞክራለን። እነዚህን ጥያቄዎች በሙሉ በአግባቡ መመለስ ግቡን ሊመታ የሚችል ታላቅ የመተባበር እንቅስቃሴ ለመመስረት ወሳንኝነት ይኖረዋል የሚል እምነት አለን። እነዚህ ጥያቄዎች "የመተባበሩን አጀንዳ በባለቤትነት ማን ያንሳው?" ከሚለው ተራ የሚመስል ጥያቄ አንስቶ የትብብሩን መነሻ፣ መሸጋገሪያና መድረሻ የሚመለከቱ ጥያቄዎችና ምላሾቻቸው በግልጽ የተካተቱባቸው ይሆናሉ። በእነዚህ ጥያቄዎች አማካይነት የትብብር ፍላጎታቸንን ገና ከጅማሮው አንስቶ የመጨረሻው ምዕራፍ እስከሚደርስ ድረስ ሊያደናቅፉት ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ተግዳሮቶች በሙሉ አስቀድመን እናነሳለን። በእነዚህም የወገናቸን የዘመናት ጥማት የሚያረካና የአገራችንን ፍላጎት የሚያሟላ በምንም አይነት ማደናቀፊያና በማንኛውም ሁኔታ ውሉን የማይስት የትብብር እንቅስቃሴ ለመፍጠር እንችላለን ብለን እናምናለን።

### 6.2 ስለ መተባበር መነጋገር

እንደኛው በርካታ የፖለቲካና ፖለቲካዊ-ያልሆኑ ድርጀቶች "በአገራችን ጉዳይ ያገባኛል" ብለው በተነሱባቸውና ውለው አድረውም የተሳካ ትብብር ለማድረግ ከቻሉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተመክሮዎች ለመማር እንደምንችለው ሌላው ቀርቶ ስለመተባበር ጉዳይ አንስተው ለመነጋገር የማይችሉባቸው ሁኔታዎች ገጥሚቸው እንደነበር ነው። በድርጅቶች ወይም በመሪዎቸ መካከል ያለው አለመግባባትና ጥርጣሬ አንዱ ለሚያደርገው ጥሪ ሌላው መልስ የማይሰጥበት ሁኔታዎች ይከሰታሉ። "ይህ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚጠራው የመተባበር ስብሰባ አስቀድሞ ለራሱ ድርጅት እንደሚጠቅም ሆኖ የተዘጋጀ ነው" በሚል መነሻ ለጥሪው መልስ አለመስጠት የተለመደ ነው። አንዳንዴም የመተባበር ጥሪውን ያቀረበውን አካል ትንሽና ዝቅተኛ አድርጎ በማየት መልስ መስጠት "የድርጅትን ወይም የመሪውን ክብር ይነካል" በሚል ምላሽ የማይሰጥባቸው ሁኔታዎች ይኖራሉ። ሌላው በአደባባይ በአንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ ለሚጠራ የእንተባበር ጥሪ መልስ መስጠት "ትብብርን ለመፍጠር መንሰፍሰፍን የሚያሳይ ምልክት ይሆናል፤ ይህም በድርድር ወቅት ይጎዳኛል" በሚል እምነት ለትብብር ጥሪ መልስ አይሰጥም።

በፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ሰፊ ልዩነት ያላቸው ቡድኖች በቀጥታ ስለትብብር መነጋገር ስለማይችሉ ንግግር እንዲጀመሩ አማላጅ እስከመላክ የሚያደርስ ፈተና ይገጥማል። ስለዚህም ነው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ኃይሎች ተገናኘተው ተባብረው እንዲሰሩ ለማድረግ ስለመተባበር የሚያደርጉትን የመጀመሪያ ስብሰባ ለመጥራት ሳይቀር ብልህነት የሚጠይቅ ስራ ሊሆን ይገባዋል የምንለው። በዚህ ረገድ የሕዝባዊ ሚዲያ ተቋማት ሚና ከፍተኛ ነው።

እንደኛው በዚህ የመተባበር ጉዳይ ላይ ጨንቋቸው የነበሩ ማኅበረሰቦች ስለመነጋገር ለመነጋገር (talking about talks) ከሚል ዝቅተኛ ደረጃ የሚጀምር የውይይትና የድርድር ሂደት ማካሄድ የሚያስፈለግበት ወቅት እንደሚኖር የሚያስተምሩትም ለዚሁ ነው። ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው በመነሳት በሁላችንም ልብ ውስጥ የሚንቦገቦገውን የመተባበር ፍላጎት እንዴት እናስጀምረው? በበኩላችን መልሱ

- ዓላማችን ሁሉንም በአገራችን ጉዳይ ያገባኛል የሚሉ ኃይሎችን ያካተተ ኅብረት ለመፍጠር ከምር ዓልሞ መነሳት ነው። በኅብረተሰባችን ውስጥ ያለውን በጣም በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝና የተሰነጣጠረና ደካማ የሲቢክ ማኅበረሰብ የእድገት ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት ይህ የመተባበር ስራ በርካታ ትናንሽ ቡድኖችንም ማካተት እንደሚኖርበት መገንዘብ ተገቢ ይመስለናል።
- የድርጅቶቹ ትልቅነትና ትንሽነት፣ ያላቸው አደረጃጀት፣ የሚታገሉለት ዓላማ፣ የሚታገሉበት የትግል ስልት አንዱን ድርጅት አካቶ ሌላውን አግልሎ ለትብብር ውይይት ለመጥራት በመስፈርትነት መቀመጥ አይኖርበትም። ማንኛውም ድርጅት የፈለገውን አቋም ይያዝ በጋራ ለመስራት ፍላጎት ማሳየቱ እንደ አንድ ትልቅ ድል ተደርጎ ሊወሰድ ይገባዋል። በዚህ ቀና ፍላጎት ላይ ቆሞ በቀና መንፈስ የሚደረግ ውይይት በሚያመጣው ውጤት ላይ ቅድመ-ብያኔ መስጠት ተገቢ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልገናል።
- ይህ ማለት ሥራቸውን ፖለቲካ ያደረጉ በተወሰነ ደረጃ የተደራጁና በተወሰነ ደረጃም የፖለቲካ ኮንስቲትዮንሲ ያላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች በቅድሚያ ተቀራርበው እንዲሰሩና ለሚፈጠረው ትልቅና ሰፊ ትብብር የፀና መሠረት እንዲሆኑ ለማድረግ የተለየ ትኩረት ሊሰጠው አይገባም ማለት አይደለም። ልንፈጥር የምንፈልገው ትብብር ቀዳሚ ዓላማ የአገራችንን ፖለቲካ ሥርዓት ለማስያዝ ቢሆንም የተለያዩ ቡድኖችን ፍላጎቶችና ጥቅሞች ከማስከበር ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው። በመሆኑም ስለ ትብብር የሚደረገው የውይይት ጅማሮ የፖለቲካ ድርጅቶችን አቀራርቦ ንግግር እንዲጀምሩ ለማድረግ ለሚሰራው ሥራ የራሱን አስተዋጽኦ ማድረግ ይኖርበታል። በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ያለውን ልዩነት አጥብቦ በጋራ እንዲሰሩ ማድረግ ከተቻለ ፖለቲካዊ ባልሆኑ በሲቪክ ድርጅቶች መካከል ሊጠብ የማይችል ምንም ልዩነት አይኖርም። ይህ ከሆነ በፖለቲካ ድርጅቶችና በሲቪክ ድርጅቶች መካከልም የሰፉ ቅራኔዎች ሊኖሩ እንደማይችል በድፍረት መናገር ይቻላል።
- በአገር ውስጥ ሆነ ከአገር ውጭ በሚገኘው ማኅበረሰብ መካከል ያለው ልዩነት በዋነኛነት የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችንና የድርጅቶችን አቋም በመደገፍ የተፈጠረ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። በሲቪክ ድርጅቶችም መካከል መተባበር መፈጠር ያልተቻለው አንዱ ሌላውን የሲቪክ ድርጅት የአንድ የፖለቲካ እምነት አራማጅና በስውር ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት ጋር ትስስር ይኖረዋል የሚል ጥርጣሬ በመኖሩ ነው። በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በፖለቲካ ፓርቲዎች መሃል መቀራረብ ሳይቻል በሲቪክ ድርጅቶች መካከል የሚደረግ መቀራረብና ትብብር ማስተባበር ፈጽሞ አይቻልም ባይባልም እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው። በፖለቲካ ርዕዮታቸው በኅብረተሰባችን ውስጥ የተለያዩ ኮንስቲቱየንሲዎ ችን ለመፍጠር የቻሉ የፖለቲካ ድርጅቶ ችን ማቀራረብና በጋራ እንዲሰሩ ማድረግ በማኅበረቡ ውስጥ ሊኖር የሚገባን ትብብር እንዲሳካ ማድረጊያው ቁልፍ መሳሪያ ነው።
- በአገራችን ጉዳይ ያገባቸዋል የሚባሉ ድርጀቶች ሁሉ ዝርዝር በማዘጋጀት አቅም በፈቀድ መንገድ ከእያንዳንዳቸው ጋር በተናጠልና በጋራ በመነጋገር ስለመተባበር ለመወያየት የሚደረግን ስብሰባ እንዴት እንጥራው በሚል ጉዳይ ላይ መመካከር ይኖርባቸዋል። ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚያግባቧቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች እንዲያነጋግሩ የሥራ ክፍፍል በማድረግ ባጭር ግዜ ውስጥ የምክክሩን ምዕራፍ ማጠናቀቅ ይቻላል።
- በዚህ ድርድር ወቅት በልምዳቸውና በሙያቸው የሚጠቅሙ በኅብረተሰቡ ውስጥ ተደማጭነት ያላቸው የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችን ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉ ግለሰቦች ማካተት አስፈላጊ ይመስለናል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## እየደመቀ የመጣው የሕዝብ የተባበሩ እሪታና . . .

(ከገጽ 3 የዞረ)

ወደ ፊት እንደምናየው እነዚህ ግለሰቦች ከምክር ለጋሽነት አልፈው ለሚተባበሩ ኃይሎች የሚጠቅሙ ሰነዶች አርቃቂና አዘጋጆች በመሆን ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል።

- በምክክሩ የተስማሙት ቡድኖችና ድርጅቶች በኤሌትሮኒክስ መሳሪያዎች በሚደረግ ኮንፈርንስ የትብብር ውይይት የሚያዘጋጅ አንድ ድርጅት ወይም ከተለያዩ ድርጅቶች የተውጣጣ አንድ ግብረ ኃይል ሰይመው የሥራን ዓይነትና የጊዜ ገደብ አስቀምጠው ለሚቀጥለው ምዕራፍ ራሳቸውን ማዘጋጀት ይችላሉ።

### 6.3 በተለያዩ ደረጃዎች የሚደረጉ ውይይቶችን ስለማድረግ

- ሁሌም ስለመተባበር የሚደረጉ ውይይቶችን ለመተባበር ምንም ችግር በሌላቸው ኃይሎች ማስጀመር ይቻላል። የሚፈለገው ሰፊ ልዩነት ያላቸውን አካላት ያቀራረበና ያካተተ ኅብረት ከሆነ ግን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው የትብብር ሥራ ልዩነት ያላቸውን ኃይሎች አቀራርቦ እንዲነጋገሩና እንዲስማሙ በማድረጉ ላይ ነው። ይህ ልዩነት ያላችውን ኃይሎች ሶስተኛ አካል በሚያደርገው ሽምግልና ወይም ተጽእኖ እንዲጀመር ማድረግ ይቻላል፤ ወይም ልዩነት አለን ከሚሉት አካላት መካከል አንዱ በተነሳሽነት ሌላውን በቀና መንፈስ በመቅረብ ውይይቱን ሊያስጀምረው ይችላል።
- ቀደም ብለን እንደጠቀስነው በማኅበረተሰባችን ውስጥ ያለው ልዩነት የሚዘወረው በፖለቲካ ድርጅቶቹ ዙሪያ ባሉ ልዩነቶች ስለሆነ በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል መኖር ለሚገባው የመተባበር ሥራ በቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይጠይቃል። እንዲህ ዓይነቱን የፖለቲካ ድርጅቶችን የማቀራረቡን ሥራ ሲቪክ ማኅበራት በተናጠል ወይም በጋር ሊያስጀምሩት ይችላሉ። ሆኖም ግን የሲቢክ ማኅበራት በጋራም ይሁን ወይም በተናጠል በአገራችን ሊፈጠር የሚገባውን የፖለቲከ ትብብር መሪዎች ወይም ማዕከሎች መሆን አይችሉም።
- ሁሉም ዓይነት ኃይሎች የሚገኙበትና የሚወያዩበት ስብሰባ ማድረግና ሁሉንም ጉዳይ ወቅቶና አበራይቶ ጉዳዩን መጨረስ የሚያጓጓ ሊሆን ይችላል። የማኅበረሰባችንን ባህልና ካለፉት የመተባበር ታሪካችን በመነሳት እንዲህ አይነቱ አካሄድ እንደማያዋጣ መረዳት ይኖርብናል። የመጨረሻው ግባችን ቀደም ብለን የጠቀስነውን ታላቅና ሁሉንም ለዴሞክራሲ የቆሙ ኃይሎች ትብብር ለመፍጠር ቢሆንም ይህ ትብብር ለመፈጠር የሚደረግ ውይይት አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ጥቂት ቡድኖች መካከል ተጀምሮ እየሰፋና እያደገ መምጣት ይኖርበታል። እነዚህን አነስተኛ ቡድኖች የየድርጀቶቹን ተፈጥሮ፣ የትግል ስልት፣ የአደረጃጀት መርህ፣ የመንቀሳቀሻ ድባብ ወዘተ በመስፈርትነት በማስቀመጥ መቦደን ይገባል። የፖለቲካና ፖለቲካዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወያኔ ህጋዊና ህግ ወጥ አድርጎ የሚያያቸው፣ የትግል ስልታቸው የተለያዩ ድርጅቶች፣ በዲያስፖራ፣ በዲያስፖራና በአገር ቤት ፣ በአገር ቤት ብቻ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ፣ በግልጽና በህቡዕ የሚንቀሳቀሱ በሚል መመደብ ይቻላል። ዞሮ ዞሮ ግን የማስተባበሩ ሥራ ሁሉም ኃይሎች ሊስማሙበት የሚገባ የጋራ ግብና የአጭር ግዜ ፕሮግራም ቀርጾ ሁሉንም በአንድ ሰፊ ትብብር ውስጥ በማካተት፣ ሁሉም በጋራ የተስማማበትን ዓላማ ግቡን እንዲመታ እንደ አንድ ኃይል ሆኖ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ነ ው።

### 6.4 ሁሉንም በጋራ የሚያስማማው የጋራ ግብ ምን ሊሆን ይችላል?

- ያለንበት ወቅት በታሪካችን ከመቼውም ግዜ የተሻለ ሁሉንም የዴሞክራሲ ኃይሎች ሊያስተባብር የሚችል ነው። ለዚህም ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው።
- የወያኔ አዋራጅ የሆነ ዘረኛ አፈና ሁሉንም የአገሪቱን ሕዝብ አዳርሷል። ሌላው ሁሉ ቀርቶ መለስ ዜናዊ የሚገለገልበት ዘረኛነት መለስን ራሱንና ጥቂት የአፈናና የዘረፋ ጓዶቹን በስልጣን ላይ ለማኖር ታስቦ እንጂ መለስ በወርቅነቱ ከሚነግድበት የትግራይ ሕዝብ መሠረታዊ የመብትና የብልጽግና ህልም ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ገሃድ ሆኗል። ባጭሩ የወያኔ የማጭበርበሪያ ጭንብሎች በሙሉ ወልቀው ከአምባገነናዊ ገበናው ጋር ርቃኑን ቆሟል። የወያኔ የማጭበርበሪያ ስልቶች ተሟጠዋል። ከእንግዲህ የሚጭበረበርለት አገራዊ ሆነ የዓለም አቀፋዊ ማኅበረሰብ የለም።
- **ይህ ወያኔ በተለይ "የ2002 ምርጫ" ብሎ ከከወነው በእብሪትና በንቀት ከተሞላ ድርጊት በመነሳት የትኛውም ተቃዋሚ ቡድን ይህንን እኩይና በሃብትና በጉልበቱ የፈረጠመን ኃይል በተናጠል ታግሎ መብቱንና ጥቅሙን ማስከብር እንደማይችል ከምር እንዲረዳ አድርጎታል።** ያለንበት ፈታኝ ወቅት የፖለቲካ ድርጅቶችንና የሲቪክ ማኅበራት ብቻ ሳይሆን፣ የፖለቲካ ድርጀቶች ለጠባብ ድርጅታዊ ዓላማቸው ማስፈጸሚያ ሲሉ ተበታተኖና አቅሙ ተዳክሞ እንዲቀር ያደረጉትን የአገሪቱን ሕዝብ ኅብረት የሚጠይቅ መሆኑ ግልጽ ሆኗል። ይህ ግንዛቤ የቆየ ቢሆንም አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ ግን ደርሶ አያውቅም።

(ክፍል 5 ሳምንት ይቀጥላል)

## ዘረኛውና አምባገነናዊው አገዛዝ በህዝብ ፊት እራሱን እንደ ልማት መንግስት አድርጎ ለመሳል የሚያደርገውን ጥረት አጧጡፎታል ተባለ

የዴሞክራሲያዊ መብት አስከባሪነት ጭንብሉ ሙሉ በሙሉ እንደወደቀበት የተረዳው ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ፣ እራሱን እንደ ልማት መንግስት ለመቅረጽ የሚያደርገውን ጥረት ማጣጧፉን ከሰሞኑ የሚደርሱን ዘገባዎች አሳይተዋል።

አገዛዙ የኢትዮጵያውያንን አመለካከት እንደ መለስ ዜናዊ ፍላጎት ለመቅረጽ እና ህዝቡ ሁሉ አንድ አይነት አለመካከት ኖሮት አብዮታዊ ዴሞክራሲን እንዲቀበል ለማድረግ የሚያካሄደውን ዘመቻ አጠናክሮ እንደቀጠለ ሐሙስ እለት መዘገባችን ይታወሳል። ከዛ ጎን ለጎን ለዝግጅት ክፍላችን የሚደርሱት ዘገባዎች እንዳሳዩት፥ ወያኔ ወጣቶች እና የመንግስት ሰራተኞች ማህበረሰቦቻቸውን ልማት እንዳለ እንዲያሳምኑ ሲጎተጉት ቆይቷል።

የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ፣ እሁድ እለት በመዲናይቱ ለስብሰባ የተጠሩ በርካታ የገዢው ፓርቲ አባላትና ካድሬዎችም ወደየማህበረሰቦቻቸው ሄደው በወያኔ አገዛዝ ስር እድገት እንዳለ ህዝቡን እንዲያሳምኑ ትእዛዝ ተቀብለዋል።

ዘረኛውና አምባገነናዊው ወያኔ ዴሞክራሲ እና የብሔረሰቦችን መብት ማስከበር የሚሉትን ጭንብሎች አጥልቆ ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ፤ በተለይም ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ በዚህ ረገድ እውነተኛ ማንነቱ ከተጋለጠ በኋላ እራሱን እንደ ልማት መንግስት ለመሳል የሚያደርገውን ጥረት ማጧጧፉ ይታወቃል። በግንቦት 15፣ 2002ቱ የምርጫ ተውኔት ደግሞ የፓርላማ መቀመጫውን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር በበርካታ ተመልካቾች ዘንድ የአንድ ፓርቲ ስርአትን በአገሪቱ ማስፈኑ ሲነገር፤ የልማት ፕሮፓጋንዳ ዘመቻውን አፋፍሞታል።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ሐምሌ 8 ቀን ባወጣው ርእሰ አንቀጽ፥ "የወያኔ ባለስልጣኖችና ዘመዶቻቸው መክበርና የፎቆቻቸው መብዛት የኢትዮጵያን እድገት አያመለክትም።" ያለ ሲሆን፥ በአገሪቱ ውስጥ የተረጋገጠ ልማት ቢኖር እንኳ፥ ልማት ማምጣት ሕዝብን የመግዛት መብት እንደማይሰጥ እና ይህንንም የቅኝ ገዢዎች አስተሳሰብ ንቅናቄው አጥብቆ እንደሚዋጋ ገልጿል።

## እንደ ወያኔ ያሉ አፋኝ አገዛዞች የህዝብ ገንዘብ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ፓይፐር በአሜሪካ ዋና ከተማ ዋሽንግተን ዲሲ ሆኖ እንዲሚገትለት በሃምሳ ሺህ ዶላር ወርሃዊ ክፍያ እንደቀጠረው ይታወቃል። በእንግሊዝ አገር በሚገኘው ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ በቅርቡ ይፋ የተደረገ የድህነት መመዘኛ፤ በኢትዮጵያ ከመቶ ሰዎች ዘጠናዎቹ ድሆች ናቸው ማለቱን መዘገባችን ይታወሳል።

## ፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ ከውጭ አገራት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በዚህም መሰረት ለድርድሩ ከሚመጡት አባቶች ውስጥ አቡነ አትናጢዮስ እና አቡነ ገሪማ በድብቅ የፓርቲያርኩ ተልኮ አስፈፃሚዎች ናቸው ሲሉ የቤተክርስቲያኒቱ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት መረጃ አስታውቀዋል።

ምንጮቻችን መረጃው እንዲታወቅ የፈለጉበት ምክንያት የውጭ አገራቱ አባቶች እንዲጠነቀቁና በተዘጋጀላቸው ወጥመድ ውስጥ እንዳይወድቁ ለማሳወቅ ነው ብለዋል።

ደጀሰላም የተባለው ድረ-ገጽ ድርድሩን በሚመለከት ባለፈው ሳምንት ባወጣው ዘገባ በሲኖዶሱ ተመርጠው ከአዲስ አበባ እንደሚመጡ ከዘረዘራቸው አባቶች ውስጥ አቡነ አትናጢዮስ ያሉበት ሲሆን፤ አቡነ ገሪማ ግን አልተጠቀሱም።

የወያኔ አገዛዝ በውጭ አገራት ሆነው የእግር እሳት የሆኑበትን ኢትዮጵያውያን ለማዳከም በሚል በኢትዮጵያ እንዳደረገው በውጭ አገራትም ቤተእምነቶችን ከቁጥጥሩ ስር ለማዋል እንደሚፈልግ ለማወቅ ተችሏል። የአባ ጳውሎስ እንቅስቃሴም የዚህ እቅድ አካል እንደሆነ ምንጮቻችን ጠቁመዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org